<u>የመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ አዋጅ ላይ የተዘጋጀ አጭር ማብራሪያ</u>

መግቢያ

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ነው። ይህን መብት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በተደራጀ ተቋማዊ ይዞታቸው ተግባራዊ የሚያደርጉት የመገናኛ ብዙሃን በአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ለመፍጠርም ቁልፍ ናቸው።ከዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አንፃርም ለዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ግንባታ፣ በአንድ አገር ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፋፋና ልማት እንዲፋጠን ጉልህ ሚና ያለው እጅግ አስፈላጊ፣ መብት ነው።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 “ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት” እንዳለው ያስቀምጣል። **በተጨማሪም ለመገናኛ ብዙሃን በተቋምነታቸው የአሰራር ነፃነት እና የተለያዩ አስተያየቶችን የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖራቸው የሕግ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ይደነግጋል። ይሁንና በሕገ መንግሥቱም ሆነ በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች** ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ጥበቃ የሚደረግለት መሠረታዊ የሆነ የሰው ልጆች ነፃነት ቢሆንም ተንቀሳቃሽ መብቶችን ለመጠበቅ እና ሌሎች ተገቢ ዓላማዎችን ለማሳካት ሲባል በሕግ የተደነገጉ እና አግባብነት ያላቸው ገደቦች ሊቀመጡበት ይችላል። ይሁን እንጂ እነዚህ ገደቦች ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ሊኖረው የሚችለውን ዘርፈ ብዙ የማይተካ ሚና ከግምት ውስጥ የሚያስገቡና የመብቱን አተገባበር አላግባብ የሚያጠቡ መሆን የለባቸውም።

ባለፉት አመታት **የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር** 533/1999” **እና የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር** 590/2000 **ን ጨምሮ መገናኛ ብዙሃንን የሚመለከቱ ዝርዝር ሕጎች ወጥተው ተግባራዊ ሆነዋል። እነዚህ** መገናኛ ብዙሃን የሚመለከቱ ሕጎች ከመፅደቃቸው በፊት በረቂቅ ደረጃ ሳሉ ጀምሮ አወዛጋቢ እንደነበሩ ይታወሳል። ሕጎቹ ታውጀው በሥራ ላይ ሲውሉ በይዘታቸውም ሆነ በአተገባበራቸው አወዛጋቢነታቸው ቀጥሏል። በተለይም ሕጎቹ “መሠረታዊ የዜጎችን መብቶችና **ነጻነቶችን አለግባብ ለመገደብና** ለማጣበብ እንዲሁም ዘርፉን ለማዳከም ምክንያት ሆነዋል” በሚል ብዙ ትችት ሲቀርብባቸው ቆይቷል።

በዚሁ መሰረት ህጎን ለማሻሻል ግለትም አዋጅ ቁጥር 533/1999 **እና አዋጅ ቁጥር** 590/2000**ን ለማሻሻል የዳሰሳ ጥናት እንዲከናወን አድርጓል። የተከናወነው የዳሰሳ ጥናት እነዚህ አዋጆች በይዘታቸው ጉድለት ያለባቸው፣ በአፈጻጸማቸው የዜጎች መብትና ነፃነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያደርሱ እንደነበር እና** ለተቆጣጣሪ አካላት የተለጠጠ ሥልጣንና ኃላፊነት የሰጡ እንደነበረ አመልክቷል። በዚህም **መሠረት ከአዋጅ ቁጥር** 590/2000 የመረጃ ነፃነትን የሚመለከቱት አንቀፆች ወጥተው እራሱን በቻለ አዋጅ ተሻሽለው እንዲወጡ በማድረግ ከአዋጁ የመገናኛ ብዙሃንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን እና **የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር** 533/1999 **በማጣመር፤ ክፍተቶችን የሚሞላ፣ ጉድለቶችን**

የሚያስተካክል፣ ግልፅ እና ለአፈጻጸም ምቹ የሆነ አዲስ ሕግ ማዘጋጀት እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ በመቅረቡ ይህ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል።

ሀ) <u>የረቂቅ ሕጉ ዓላማና ግብ</u>

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በራሱ ሰብዓዊ መብት ከመሆኑ ባሻገር ለሌሎች መብቶች ማስፈጸሚያ መሳሪያም **ነው። ስለዚህም ሀገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ** ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን የሚያስከብር፣ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብን ለመፍጠር የሚያግዝ፣ የመገናኛ ብዙሃን ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። **ስለሆነም የተዘጋጀው ረቂቅ ሕግ ዓላማና ግብ የሚከተሉት ናቸው፡-**

- በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና በኢትዮጵያ ላይ ግዴታ በሚጥሉ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ እንዲረጋገጥ የሚያስችል ምቹ የሕግ ማዕቀፍ መፍጠር፤
- ጥራቱ የተጠበቀ፣ ተደራሽ፣ እና አስተማማኝ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት እንዲስፋፉ ለማድረግ የሚያስችሉ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የምዝገባ እና የቁጥጥር ሥርዓትን መዘርጋት፤ እና፣
- መገናኛ ብዙሃን ተግባራቶቻቸውን በሕግ መሠረት እንዲያከናውኑ ለማድረግ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፣ መገናኛ ብዙሃንን የሚያስተዳድረው የመንግሥት አካል ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን ማድረግ።

ለ) <u>የተከናወኑ ቅድመ ማርቀቅና ድህረ ማርቀቅ ተግባራት</u>

ረቂቅ ሕጉ ከመዘጋጀቱ በፊት የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ለማማከር የተቋቋመው የሕግና ፍትሕ አማካሪ ምክር ቤት በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው ያሉ የሕግ ባለሙያዎችን ያቀፈ አራቱን የቻለና 14 አባላት ያሉት **የጥናት ቡድን በማዋቀር** ይህንን ሕግ በሚመለከት **የችግሮች ማመላከቻ የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል። የዳሰሳ ጥናቱ** ውጤትም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና የኅብረተሰብ ክፍሎች ለተውጣጡ ተሳታፊዎች ቀርቦ ውይይት ተደርጎ ግብዓት እንዲሰጥበት ሆኗል። ጥናቱ ዳብሮ ከተጠናቀቀ በኋላ **ረቂቅ አዋጁን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎችን በማደራጀት የመጀመሪያው ረቂቅ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።**

ረቂቁን በማዘጋጀት ሒደት በነባሩ ሕግ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች፣ **በዳሰሳ ጥናቱ የተለዩ** የሕጎቹን ጥንካሬና ክፍተቶች በመለየት እና የሕጎቹ ያለፉት አመታት አተገባበርን በመዳሰስ፣ መሻሻልና መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች ለማሻሻልና ለማስተካከል ተሞክሯል። ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችና ምርጥ ተሞክሮ ያላቸው የሌሎች ሀገራት ልምድ እንደ ግብዓት

ተወስዷል። ከአፍሪካ የደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ኬንያ፣ ቦትስዋና እና ናይጀሪያን ልምድ ለማየት ተችሏል። ከአፍሪካ ሀገራት በተጨማሪ እንደ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ስዊዲን እና እንግሊዝን የመሳሰሉ ሀገሮችን ልምድ እንደአግባብነቱ ለማየት ተሞክሯል። የረቂቅ ሕግ አዘጋጅ ቡድኑ የተባበሩት መንግሥታት የብሮድካስት ሕግን በሚመለከት ያወጣቸውን ሞዴል ሕጐችና የቁጥጥር አሰራሮችን አይቷል።

በረቂቁ ላይ ተከታታይ የምክክር መድረኮች በማድረግ የተሰጡ አስተያየቶች እና መረጃዎች ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በተለይም ሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍል አስተያየት እንዲሰጥበት የረቂቅ አዋጁ ኮፒ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ ስለተለቀቀ ማንኛውም ዜጋ በረቂቅ አዋጁ ላይ ያለውን አስተያየት የሚያቀርብበት መንገድ ተመቻቶ ግብዓት ተገኝቶበታል። **ከሕግ ባለሙያዎች፣** ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት፣ ከመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶችና አመራሮች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ከክልል መገናኛ ብዙሃን አመራሮች ጋር ከተዘጋጁ የውይይት መድረኮች በተጨማሪ በክልል ደረጃ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት አስተያየት እና ሀሳብ እንዲያካፍሉ በሐዋሳ እና በድሬዳዋ ከተማ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ የሚመለከታቸው አካላት እንዲሳተፉ ተደርጓል። በዚህ ሒደት በተለይም ከብሮድካስት ባለሥልጣን አዲስ አመራርና ከመገናኛ ብዙሃን ኃላፊዎች ጋር በቅርበት በመመካከር ግብዓት ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል። ከአጋዥ አካላት በተገኘ ድጋፍም የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ልምድና እውቀት ያላቸው የውጭ ሃገር ባለሙያዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ተደርጓል። **እነዚህን ግብዓቶች በማካተት ይህ የመጨረሻው ረቂቅ ተዘጋጅቷል።**

ሐ) <u>የረቂቅ አዋጁ ቅርጽና ይዘት</u>

1) <u>ቅርጽ</u>

ረቂቁ በአጠቃላይ በሰባት ክፍሎች የተዋቀረ እና 91 አንቀፆችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ስለአጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ እና ስለአዋጁ አፈጻጸም የተመለከቱ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን፤ክፍል ሁለት ስለመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ክፍል ሶስት ስለመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት፣ ምዝገባና ፈቃድ፤ ክፍል አራት ስለመገናኛ ብዙሃን መብቶችና ግዴታዎች፤ ክፍል አምስት ስለአስተዳደራዊ እርምጃዎች፤ ክፍል ስድስት የመገናኛ ብዙሃን ኃላፊነትና ሕጋዊ ተጠያቂነት፤ እና ክፍል ሰባት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው።

***መሠረታዊ* መርሆችን የያዙ ድንጋጌዎች በየክፍሉ መግቢያ ላይ ተካተዋል። እነዚህ ድንጋጌዎች የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶችና ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚመሩበትን መሠረታዊ መርሐችን ያስቀምጣሉ። ድንጋጌዎቹ አስገዳጅ ባይሆኑም በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በተቆጣጣሪው ባለሥልጣንና በፍርድ ቤቶች የሚተረጎምባቸውን መሠረታዊ አቅጣጫዎች ለማመላከት የታለሙ ናቸው።**

2) <u>ይዘት</u>

በአዋጁ መግቢያ የሕጉ ዓላማ ምን እንደሆነ እና የመገናኛ ብዙሃንን የሚመለከት በስራ ላይ የነበሩ ሕጎች የነበረባቸውን ክፍተቶች ማስተካከል ማስፈለጉ በጥቅል አገላለጽ ተቀምጧል። በሕገ መንግሥቱ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ ግዴታ የሚጥሉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ፤ እና ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚጣጣም ሕግ የማውጣት አስፈላጊነትን መንግሥት እንደሚገነዘበው ተመልክቷል። **የሕጉ ዓለማም** ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን አሠራር እንዲስፋፋ በማድረግ ለሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ፣ በሕግ መሠረት እና ኃላፊነት በሚሰማው መልኩ የሚንቀሳቀሱ መገናኛ ብዙሃን እንዲስፋፉ ማድረግ **እንደሆነ ተመላክቷል።**

በክፍል አንድ የአዋጁን አጭር ርእስ፣ ትርጓሜ እና የተፈጻሚነት ወሰንን ያካተተ ነው። የአዋጁ **አጭር ርዕስ "የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር .../2012" የሚል ሲሆን፤ነባሮቹ አዋጆች "የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር** 533/1999" **እና "የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር** 590/2000" **የሚሉ ናቸው።። የተደረገው ለውጥ የአዋጁ የተፈፃሚነት ወሰን በየጊዜው የሚወጡ ሳትመቶች፣ ብሮድካስት አገልግሎት እና የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን በመሆኑ ይህንን ሊያሳይ በሚችል መልኩ እንዲቀረጽ መደረጉ ነው።።**

በሥራ ላይ ባሉት አዋጆች ውስጥ የአንዳንድ ትርጓሜዎች ግልጽ ያለመሆንና የድንጋጌዎች በበቂ ሁኔታ አለመካተት እንደ ትልቅ ተግዳሮት የሚቆጠር ነበር። **የረቂቁ** *አንቀፅ* 2 *ትርጉም* **የተሰጣቸውን ቃላት እና ሐረጋት በውስጡ የያዘ ሲሆን ከአዋጅ ቁጥር** 533/1999 **እና** 590/2000 **ሲነጻጸር እንደ አዲስ የተተረጎመ፣ ትርጉማቸው የተሻሻለ እና ከትርጉም እንዲወጡ የተደረጉ ቃላትና ሐረጋት አሉ።። ለምሳሌ** "የመገናኛ ብዙሃን"፣ "የብሮድካስት አገልግሎት"፣"ፕሮግራም"፣ "የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት"፣ "አሳታሚ"፣ እና "አታሚ"፣ **የሚለው በነባሩ ከነበራቸው ትርጉም ተሻሽሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል።። ይህም የሆነው በነባሩ የነበራቸው ትርጉም ግልጽ ባለመሆኑ ወይም አለግባብ የተቀመጠ ትርጉም የነበራቸው በመሆኑ ነው።።**

ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 590/2000 "የመገናኛ ብዙሃን" በየጊዜው የሚወጡ ሳትመቶችንና ብሮድካስቶችን የሚያካትት የሳትመት ስራ ነው የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። ይሁንና "የመገናኛ ብዙሃን" እና "የሳትመት ስራ" ትርጉም ልዩነታቸውን በግልፅ የሚያሳይ አለመሆኑ፣እንዲሁም በአዋጁ ትርጉም ሳይሰጠው የተካተተው "ሳትመት" ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚያምታታ ነበር። በተጨማሪም በአዋጁ የነበረው የመገናኛ ብዙሃን ትርጉም እጅግ ሰፊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው አሰራሮች ጋር የሚጋጭ ነው። በበርካታ ዴሞክራሲያዊ ሃገሮች ትያትር፣ ሲኒማና መጻሕፍት እንደ መገናኛ ብዙሃን አይቆጠሩም። አዋጁ በዋነኛነት የተዘጋጀው መገናኛ ብዙሃንን ለማስተዳደር በመሆኑ ሌሎች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት መገለጫዎች ላይ ተፈጻሚ ማድረግ አላስፈላጊ ጫና ይፈጥራል። በዚሁ መሠረት ረቂቁ አዋጅ "የመገናኛ ብዙሃን" ትርጉምንም ያሻሻለ ሲሆን "የብሮድካስት አገልግሎት" በአዋጅ ቁጥር 533/1999 ከተሰጠው ትርጉም በተሻለ አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውንና የሚገኝባቸውን መንገዶች እና የማያካትታቸውን አገልግሎቶች በመጨመር የተሻሻለ ትርጉም ተሰጥቶታል።

አዳዲስ ትርጉሞች በሚሰጡ ጊዜ በአዋጁ በተለየ ሁኔታ ትኩረት የተሳጣቸው ጉዳዮች ላይ ግልፅነት እንዲኖር ለማድረግ የታለመ ሲሆን በተለይ ቁጥጥር የነበረውን አሉታዊ ስሜት ለመለወጥ ምን ምን እንደሚያካትና ይህ ሥራ በየጊዜው በሚወጣ ጎትመት ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ተመልክቷል። ከእነዚህም ውስጥ "የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን"፣ "ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት"፣ “ማኅበረሰብ”፣ “ሃገር በቀል ይዘት”፣ “ቁጥጥር”፣ "የመገናኛ ብዙሃን የእርስ በእርስ ቁጥጥር"፣ "የመረጃ ብዝሃነት"፣ "የሕዝብ ጥቅም"፣ እና "የባለድርሻ አካላት ምክክር" **የሚሉት ይገኙበታል።** ለምሳሌ በረቂቁ "የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን" ማለት በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ሥር ዋነኛ ሥራው ዜናና ፕሮግራምን መሰብሰብ፣ ማዘጋጀት፣ ማጠናቀርና ማሰራጨት በሆነ ድርጅት በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ምስል፣ ድምፅ፣ ቪድዮ እና የድረ-ገፅ ፅሁፍን በመጠቀም ወይም እነዚህን በማቀናጀት መረጃ የማስተላለፍ አገልግሎት እንደሆነ ተደንግጓል። ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ላይ ትኩረት የተደረገው ይዘት ለመምረጥና ለመሰደር ምንም አይነት ሥርዓት የማይዘረጉ እንደ ፌስቡክና ትዊተር ያሉ ማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃንንና ጦማሮችን ላለማካተት ነው።

በሁለቱ አዋጆች የትርጉም ክፍል ተካተው የነበሩት "አከፋፋይ"፣ "አስመጪ"፣ "ማስታወቂያ"፣"የፖለቲካ ድርጅት"፣ **እና** "ኢንስፔክተር" **መተርጎማቸው አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲወጡ ተደርገዋል።**

አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰንን **የሚያስቀምጥ ነው። በዚህም በዋነኛነት** በራዲዮና በቴሌቪዥን አማካኝነት ከውጭ አገራት የሚሰራጩ ጎትመቶችን እና የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራሞችን በሕግ ከመቆጣጠር አንፃር **የነበረውን ክፍተት ለማስቀረት ተሞክሯል።** በዚህ አዋጅ መሠረት ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚታተም በየጊዜው የሚወጣ ጎትመት፤እና ከሃምሳ በመቶ በላይ ይዘቶቹ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮሩ፣ አገልግሎቱን ለኢትዮጵያዉያን አድማጭና ተመልካቾች በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚያቀርብ እና ገቢውን በአገር ውስጥ ከሚገኝ ማስታወቂያና ድጋፍ የሚያገኝ የብሮድካስት አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ የሚሆንበት አሰራርን ይዘረጋል።

በዚህም መሠረት ረቂቅ አዋጁ ከሃገራዊ ይዘት፣ ቋንቋና ገቢ አንፃር ከሃገራቱ ጋር ቁርኝት ያላቸውን የብሮድካስት አገልግሎቶች ሕግ ጥሰው ሲገኙ ተጠያቂ የሚደረጉበትን አሰራር ይዘረጋል። ይሁንና ይህ ድንጋጌ ከተፈጻሚነት አንፃር ተግዳሮት ሊገጥሙት ይችላሉ። እንደ ኬብልና ሳተላይት ያሉ ማሰራጫዎችን የሚጠቀሙና ከሃገር ውጭ የሚገኙ የብሮድካስት አገልግሎቶችን መቆጣጠርና በአዋጁ የተጣሉ ግዴታዎችን እንዲያከብሩ ማድረግ ከአፈፃፀም አንፃር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከጉዳዩ አስፈላጊነት አኳያ የሳተላይት ሥርጭቶች የሃገራትን ሕጎች በሚጥሱበት ጊዜ ይህን ለማስቆም የአገልግሎቱ መቀበያ መሳሪያዎችን መከልከል፣ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማቱን በሕገወጥነት መፈረጅና በዝቅተኛ የይዘት ደረጃዎች ላይ አለም አቀፋዊ ስምምነት ማድረግን ጨምሮ ሃገራት የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። ስለዚህም በአዋጁ ተፈፃነት ወሰን ውስጥ መካተታቸው ድርጅቶቹ ሕግን አክብረው እንዲሰሩ የተጣለባቸው ግዴታ እንዳለ በግልጽ እንዲገነዘቡና ሕግ የጣሱ ግለሰቦችንና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትን ተጠያቂ ለማድረግ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያስችላል ተብሎ ታምኖበታል።

የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሁለት የዘርፉን አስተዳዳሪ አካል አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር **የያዘ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በተቆጣጣሪ አካሉ ስያሜ፣ አሰያየም እና ሥልጣን እና ኃላፊነቶች ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ረቂቅ አዋጁ ቀድሞ የነበረውን የብሮድካስት ባለሥልጣን የሚለውን ስያሜ አዲስ ከተሰጠው ሁሉንም የመገናኛ ብዙሃን ዘርፎች የመከታተልና የመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነቱ ጋር በማጣጣም ስያሜው ተቀይሮ ‹‹የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን›› ተብሎ እንዲሰየም ተደርጓል፡፡ ይህ ከሌሎች አገራት አቻ ተቋማት አሰያየም ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡**

በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት የባለሥልጣኑ ገለልተኝነት ችግር በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተነስቷል፡፡የመገናኛ ብዙሃንን የሚቆጣጠሩ መንግሥታዊ አካላት በተቻለ መጠን ከአስፈፃሚው አካል ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው አለም አቀፍ መርሆዎች ያስቀምጣሉ፡፡ ገለልተኝነታቸውን የማረጋገጫ አንደኛው መንገድ ተጠሪነታቸው ለአስፈፃሚው እንዳይሆን ማድረግና በሚዋቀሩበት ጊዜም አባላቶቻቸው ከአስፈፃሚው ቁጥጥር ነፃ በሆነ መልኩ እንዲመደቡ ማድረግ ነው፡፡ የቀድሞው ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከፈረሰ በኋላ የብሮድካስት ባለሥልጣን ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኗል፡፡ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ይሄንን በመቀየር የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበሩት አዋጅ እና ደንቦች የባለሥልጣኑን ቦርድ ጨምሮ የባለሥልጣኑ አመራር አመዳደብ የባለሥልጣኑን ነፃነትና ገለልተኝነት በበቂ ሁኔታ አላስጠበቀም የሚል ቅሬታ በተለያዩ የባለድርሻ አካላት ዘንድ ይንፀባረቃል፡፡ በተለይም የቦርዱ አባላት የሚመለመሉበት ግልፅ አሰራር ባለመኖሩ፣ የቦርዱ አባላት የአሿሿም ሥርዓት በበቂ ሁኔታ የባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ አለመሆኑ፣ የቦርዱ አባላት በስራቸው ላይ ሳሉ አግባብ ካልሆነ ተፅዕኖና ግፊት የሚጠበቁበት ሁኔታ ስላልተመቻቸ የቦርዱ ነፃነትና ገለልተኛነትን አጠያያቂ አድርጎታል፡፡ በዚህ ረቂቅ አዋጅ የቦርዱን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ሙያዊ ብቃትና አቅም ያላቸው፣የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም ተቀጣሪ ያልሆኑ፣ መልካም ሥነ-ምግባር እና ስብዕና ያላቸው፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰየሙ ዘጠኝ አባላት እንዲኖሩት የተደረገ ሲሆን የቦርድ አባላት እጩዎችን የመመልመሉና የማፅደቁ ሒደት ለሕዝብ ግልፅ በሆነና አሳታፊ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከቦርዱ አባላት መካከል ሁለቱ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ሁለቱ ከመገናኛ ብዙሃን እና ሁለቱ ለመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ጠቀሜታና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ ተቋማትና የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ ሦስቱ ጠቀሜታና አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት፤ የተውጣጡ እንዲሆኑ በማድረግ ሚዛናዊ የሆነ ለሕዝብ ጥቅም የቆመ ውሳኔ ሰጪ አካል ለመመስረት ታልሟል፡፡

የቦርድ አባላትን ብቻ ሳይሆን የባለሥልጣኑን አመራሮች ከፖለቲካዊ ተፅዕኖ ለመጠበቅ በረቂቁ የባለሥልጣኑ ዋና እና ምክትል ዳይሬክተሮች ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የባለሥልጣኑ ዋና ዳሬክተርም በቦርዱ ተመልምሎ እንዲሰየም ተደርጓል፡፡ **ረቂቁ ባለሥልጣኑን ከኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመጠበቅ በ**ዋና ዳይሬክተር፣ በምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ በቦርድ አባል፣ ወይም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን **የጥቅም ግጭት መርህም ይደነግጋል፡፡**

ከዚህ ቀደም በነበረው አዋጅ የቦርዱ አባላት የሥራ ሁኔታና የሥራ ዘመን አልተደነገገም፡፡ በረቂቅ አዋጁ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የቦርዱ አባላት አሿሿም በተለያየ ጊዜ እንዲሆን (Staggered appointment) ተደርጓል፡፡ ይህም የቦርድ አባላት በሙሉ በአንድ ጊዜ የሚለወጡ ከሆነ ቦርዱ ተቋማዊ ትውስታ

(institutional Memory) እንዳያጣና ልምድ ያካበቱ የቦርድ አባላት ለአዳዲስ አባላት እንዲያስተላልፉ ለማድረግ ያስችላል። የቦርዱን አባላት ነፃነት ለማጠናከርም ግማሽ የቦርድ አባላት በድጋሚ ለመሾም የማይችሉ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የቦርዱን አባላት ነፃነት ከማስጠበቅ አንፃር በረቂቅ አዋጁ የቦርድ አባል የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ምክንያቶችን በግልፅ በማስቀመጥ እነዚህ ምክንያቶችና የተዘረጋው ሥርዓት በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የቦርድ አባላትን ከኃላፊነታቸው እንደማይነሱ ጥበቃ በመስጠት ነፃነታቸውንና ገለልተኝነታቸውን ያጠናክራል።

በነባሩ አዋጅ ለባለሥልጣኑ የተሰጠው እጅግ የሰፋና ለትርጉም የተጋለጠ ሥልጣን ነው በሚል ቅሬታ ይቀርብ ነበር። ከዚህ ቀደም ከነበረው አዋጅ በተጨማሪም ሥልጣንና ኃላፊነት የሚደነግጉ ተጨማሪ ደንቦች መኖራቸው ጉዳዩን ይበልጥ ውስብስብ አድርጎታል። **ከእነዚህ ባለሥልጣኑ በተለያዩ ሕጎች ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል አብዛኛዎቹ በረቂቅ አዋጁ እንዲካተቱ ተደርገዋል። ለምሳሌ ከቀድሞ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ፅ/ቤት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል ለውጭ የመገናኛ ብዙሃን የዘገባና የዜና ወኪሎች ድጋፍ መስጠት የባለሥልጣኑ ተግባር እንዲሆን ተደርጓል።**

በነባሩ ሕግ ላይ የባለሥልጣኑ ዓላማዎች በአመዛኙ ቁጥጥር ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ለባለሥልጣኑ የተቀመጡት ዓላማዎች እንዲለወጡ ተደርጎ ይልቁንም ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ማብቃትና እንደ አስፈላጊነቱም መቆጣጠር ላይ በሚዛናዊነት እንዲያተኩር ተደርጎ ዓላማው ተቀርጿል። በተለይም ባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃንን የእርስ በእርስ አስተዳደር መዋቅር ለመደገፍና አብሮ ለመስራት የሚያስችል ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ረቂቁ የብሮድካስት አገልግሎትን በሚመለከት ባለሥልጣኑ ያለው የስራ ኃላፊነት ተመሳሳይ ሥልጣን ካለው የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣን ጋር በመሆን በጋራ እንደሚሰራ ይደነግጋል። ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ ሁኔታን የሚወስን፣ ፈቃድ የሚሰጥ፣ የሚያድስ፣ የሚያግድና የሚሰርዝ ቢሆንም ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውለውን የሬዲዮ ሞገድ የሚያስተዳድረው የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣን ነው። በመሆኑም ረቂቁ ከኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ለብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የሬዲዮ ሞገድ እንዲመደብ እንደሚያደርግና ሥልጣንና ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዳስፈላጊነቱ ከኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣን ጋር በትብብር እንደሚሰራ ይደነግጋል።

ክፍል ሶስት የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት፣ ምዝገባና ፈቃድን በሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን ከነባር አዋጆች በተለየ አዳዲስ ድንጋጌዎች የገቡ ሲሆን አብዛኞቹ ድንጋጌዎች እንዲስተካከሉ እና ግልፅ ሆነው እንዲቀመጡ ተደርጓል።

በረቂቁ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ገደቦች የተለያዩ የጎበረተሰብ ክፍሎች ለመገናኛ ብዙሃንና ለሚያስተናግዷቸው የተለያዩ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች ተደራሽ እንዲሆኑ እንዲያስችሉና የሃሳብ ብዝሃነትን በማረጋገጥ ለዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ግንባታ አስተዋፅኦ በሚያደርጉበት መልኩ እንዲሻሻሉ ተደርጓል።

በነባር አዋጆች **አንድ ግለሰብ ብቻውን የመገናኛ ብዙሃን ሊያቋቁም የሚችልበት አሰራር በመከልከል** የብሮድካስት አገልግሎት ስራን፣ በየጊዜው የሚወጡ ጎትመቶችን ወይም የዜና አገልግሎት ስራን በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንዲሰራቸው ተደንግጎ ነበር። **ዜጎች ራሳቸውን ችለው በግለቸው** የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነትን መሥፈጋቸው የመስራት መብትን ከመገደቡም በላይ፣ በሌሎች የንግድ ባለቤትነት ላይ ያልተጣለ ክልከላን በማስቀመጥ **ዘርፉን**

ለማስፋፋት እንቅፋት ሲሆን ታይቷል። በዚህ ረቂቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል በየጊዜው የሚወጣ ኅትመት እና የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን በባለቤትነት ለማቋቋም እንደሚችል በመደንገግ ማሻሻያ ተደርጓል። ነገር ግን የብሮድካስት አገልግሎት ስራን በሚመለከት ግለሰባዊ ተጠያቂነትን ለማስወገድና ሥራውን በተደራጀ መልኩ የመስራትን አስፈላጊነት እና በአለም አቀፍ ተሞክሮም እንደታየው ባለቤትነቱ ሕጋዊ ሰውነት ለተሰጠው አካል ሆኖ እንዲቀጥል ተድርጓል።

ነባር ሕጎች መገናኛ ብዙሃንን በባለቤትነት የመመስረት መብትን ለኢትዮጵዊያ ዜጎች ብቻ ይሰጡ ነበር። ለዚህ አግባብ አንድ ኩባንያ ኢትዮጵያዊ ኩባንያ ነው የሚባለው የኩባንያው የካፒታል ምንጭ ሙሉ በሙሉ ከአገር ውስጥ የሆነ እና የአክስዮኑ ባለድርሻዎች በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ሲሆን ነው። የውጭ አገር ሰዎች የአክስዮን ባለድርሻዎች የሆኑበት ድርጅት አክስዮን የያዘበትን ኩባንያ የማያካትት ሆኖ በመደንገጉ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ሰው በመገናኛ ብዙሃን ሥራ የመሰማራት መብት አልነበረውም። ይህም መገናኛ ብዙሃን የቴክኖሎጂ ልውውጥ እንዳያደርጉ እና ተስፋፍተው በካፒታልና በእውቀት ተጠናክረው እንዳያድጉ አሉታዊ ተፅእኖ የነበረው ከመሆኑም በላይ በተለይም ዜግነትን መሰረት ያደረገ የተለጠጠ ገደብ ያደርጋል። በተለይም ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን በዘርፉ በሕጋዊ መንገድ እንዳይሳተፉ በማድረግ ከውጭ አገር ፈቃድ አግኝተው የአገር ውስጥ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሳያገኙ በአገር ውስጥ ቋንቋ በሳተላይት የቴሌቪዥን አገልግሎት የሚሰጡ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲበራከቱ አድርጓል።

በሌላ በኩል የብሮድካስት አገልግሎት በውጭ ፍላጎቶች ቁጥጥር ሥር እንዳይሆኑ የውጭ ዜጎችን ያልተገደበ ባለቤትነት መከልከል ብሔራዊ ጥቅምንና የሀገር ሉዓላዊነትን ከማስከበር አንፃር አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ለሀገር በቀል ንግድ ጥበቃ ለማድረግ እና ዘርፉ የደንበኛውን ባህል በሚያውቁና በሚያከብሩ አካላት እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ዘርፉን ሙሉ በሙሉ ለውጪ ዜጎች መክፈት ነባራዊ ሁኔታው አይፈቅድም። በመሆኑም በረቂቁ የውጭ ዜጎች ውስን (ከ25 በመቶ የማይበልጥ) አክስዮን እንዲኖራቸው በማድረግ በመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት እንዲሳተፉ ተደርጓል። ይህም ዘርፉ የሚፈለግበትን አገልግሎት ለማቅረብ እንዲችል በኢንቨስትመንትና በሌሎች ድጋፎች አቅም እንዲያጎለብት፣ የቴክኖሎጂና የክህሎት ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆን ያስችለዋል ተብሎ ይገመታል።

በነባር ሕጎች በግልፅ ባይቀመጥም ነባር አሳታሚ ኩባንያዎች የተጨማሪ ኅትመት ምዝገባ ጥያቄ በአፈጻጸም የተከለከለ ከመሆኑ ባሻገር የጋዜጣና መፅሄት አሳታሚዎች በተመሳሳይ ስያሜ የሚታተሙ የ1 ጋዜጣና 1 መፅሄት ባለቤት እንዳይሆኑ መከልከላቸው በዘርፉ እድገት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ በጥናቱ ተረጋግጧል። በዚህ ረቂቅ የኅትመት የመገናኛ ብዙሃንን በማስፋፋት የሃሳብ ብዝሃነትን እና የመረጃ ተደራሽነትን በማሳደግ ረገድ ጠቀሜታ ስላለው ይህ ድንጋጌ እንዲሻሻል በመደረጉ አንድ አሳታሚ ያለገደብ ኅትመቶች ሊኖሩት ይችላሉ።

የመገናኛ ብዙሃን አንዳንድ አካላት አለስፈላጊ የመገናኛ ብዙሃን **የበላይነትና ክምችትን በጠቅላይነት በመቆጣጠር የመረጃ ምንጮችንና የሃሳብ ብዝሃነትን እንዳይጎዱ ለማድረግ የሚያስችሉ አንቀፆች በረቂቁ ተካተዋል። ጠቅላይነትን ከመከላከል አንፃር፣ በሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደታየው የባለቤትነት ድርሻን** (የደንበኛ፣ የገበያ ወይም የተፅዕኖ) ወይም በባለቤትነት ሊያዙ የሚችሉ የመገናኛ ብዙሃን ብዛትን መሠረት ያደረጉ ገደቦች ሊወጡ ይችላሉ። በዚህ ረቂቅ የመገናኛ

ብዙሃንን እድገት በማይገድብ መልኩ ጠቅላይነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ብዛትን እና ድርሻን በሚመለከት ደግሞ ውጤታማ ቁጥጥርን በማቀናጀት የባለቤትነት ገደብ ተግባራዊ እንዲደረግ ተደንግጓል።

በባለቤትነት የሚያዙ የመገናኛ ብዙሃን ብዛትን በሚመለከት በነባር ሕጎች የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ወይም ከአንድ በላይ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሆኖ ለቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ሌላ ፈቃድ የሚጠይቅ ድርጅት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጠውም። ይሄንን በማሻሻል በረቂቅ አዋጁ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት አንድ ቴሌቪዥን፣ አንድ ሬዲዮ፣ አንድ ጋዜጣ፣ አንድ መፅሔትና አንድ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም እንደሚችል ይደነግጋል። ከዚህ በተጨማሪ ውጤታማ ቁጥጥር የሌለው ድርሻ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ላይ እንዲኖረው ይፈቅዳል።

ድርሻን ለመወሰን የውጤታማ ቁጥጥር ገደብ ማድረግ የተለመደ ቢሆንም በነባር ሕጎች ውጤታማ ቁጥጥርን በተመለከተ የተካተቱት ድንጋጌዎች ግልፅነት የሚጎላቸውና የገበያ ድርሻንና መቶኛን አቀላቅለው የያዙ፣ በተግባርም ዘርፉ ላይ ተፅዕኖ የፈጠሩ ናቸው። ረቂቁ ውጤታማ ቁጥጥርን ለመለካት የመቶኛ ድርሻ ስሌትን ብቻ ይጠቀማል። ይህም ቀላልና የባለቤትነት ገደቦችን ባልተገባ መንገድ ለመጠቀም ብዙም በር የሚከፍት ባለመሆኑ ነው። የገበያ ድርሻ በተቃራኒው ውስብስብና የሚፈለገውን ውጤት የማያመጣ ሆኖ ተገኝቷል። በነባሩ አዋጅ ከ15 በመቶ በላይ የያዘ ማንኛውም ሰው ውጤታማ ቁጥጥር እንዳለው ሲገመት የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ በመቀመርና የሀገራችንን የአክሲዮን ኩባንያዎች እድገት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአዲሱ ረቂቁ አዋጅ ወደ 25 በመቶ በላይ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

በረቂቁ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን በየሦስት አመቱ የመገናኛ ብዙሃንን ይዞታ እና የመገናኛ ብዙሃን የገንዘብና የገበያ እንዲሁም የባለቤትነት ይዞታን ከገበያና ከሃሳብ ጠቅላይነት አንጻር በመገምገም በአዋጁ የተደነገገው የባለቤትነት ገደብና የአክሲዮን ድርሻ ላይ ለውጥ የማድረግ ነፃነት ተሰጥቶታል። ይህም የተደረገው የባለቤትነት ገደቦችን በሙሉ በሕጉ ከመደንገግ ይልቅ ባለሥልጣኑ ከዘርፉና ከኢኮኖሚው ይዞታ ተለዋዋጭነት አንፃር በሒደት እየወሰነ እንዲሄድ ነፃነት መስጠት የተሻለ ውጤታማ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

የብሮድካስት ፈቃድ የማይሰጣቸውን አካላት በሚመለከት በነባር ሕጎች እንደተቀመጠው የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሃይማኖት ተቋማት ፈቃድ አይሰጣቸውም። ይሁንና ቴክኖሎጂው ከፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተነሳ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮና በበይነመረብ የብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጡ የሃይማኖት ተቋማት ቁጥር እየበዛ መጥቷል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ክልከላ በዋነኛነት የፖለቲካ ሚዛን ለመጠበቅ የታለመና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በዚህ ረቂቅም ክልከላው ተጠብቋል። ይሁንና የሃይማኖት ተቋማትን በተመለከተ ግን ውስን በሆነው እና እጥረት ባለበት የሬዲዮ ሞገድ የነበረው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች ማሰራጫ መንገዶች ግን ፈቃድ አግኝተው እንዲያሰራጩ ተፈቅዶላቸዋል።

ከአፈፃፀም አንፃር የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ልዩ የሕዝብ ጥቅም ያለበት በመሆኑ የባለቤትነት ገደቦች ሊወጡና ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገባው በመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካላት ነው የሚለው አቋም በርካታ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ የሕግ ማዕቀፍ ያላቸው አገራት የሚጋሩት ነው። በመሆኑም በረቂቁ የባለቤትነት ሁኔታን በግልፅ ለተቆጣጣሪው አካል የማሳወቅ ግዴታ

በማስቀመጥ፣ ግዥና መጠቅለልን ጨምሮ የመገናኛ ብዙሃን የባለቤትነት ለውጥ ሲኖር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅና ማስፀደቅ እንደሚገባ ተደንግጓል።

የመገናኛ ብዙሃን ምዝገባን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በአንዳንድ ሀገራት እየቀሩ ነው። አብዛኛዎቹ አገራት የተለየ የምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት ሳያስፈልጋቸው የጋዜጣና መፅሄት አሳታሚዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ መሠረት እንደማናቸውም የንግድ መስኮች ከንግድ ፈቃድ ሰጪ አካል ፈቃድ በማግኘት ብቻ እንዲሰማሩ ያደርጋሉ። በነባር ሕጎች ከአንድ ክልል በላይ የሚሰራጩ የግል/የንግድ ጋዜጣና መፅሄቶችን ለማሳተም የሚፈልግ አሳታሚ በማስታወቂያ ሚኒስቴር በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይጠበቅበታል። ይህ የምዝገባ ሥርዓት አስፈፃሚው አካል ከተዋቀረበት መንገድ በተነሳ ለፖለቲካ ተፅእኖ የተጋለጠ እንደሆነ ይጠቀሳል። በተግባርም ለአንዳንድ አካላት የሳትመት ፈቃድ እንዳይሰጥ፣ የሌሎች እንዳይታደስ እና አለግባብ እንዲታገድ በማድረግ ተቆጣጣሪ ተቋማት የዘርፉ ተዋንያንን እንዲያንገላቱ ሰፊ እድል መፍጠሩ ታይቷል።

ይሁንና የሳትመት እና የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን ምዝገባ የስም ድግግሞሽ እንዳይኖር፤ የአክሲዮን ድርሻና የባለቤቶችን ማንነት ለማወቅ እና የሳትመት ውጤቶችን ስርጭት የሚያሳዩ መረጃዎች ለማጠናቀር አስፈላጊ በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ እንዲቀር አልተደረገም። በረቂቁ ገለልተኛ ሆኖ የተቋቋመው የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንዲከናወን መደረጉ ምዝገባን በመጠቀም የሚፈጠሩ ጫናዎችን ለማስቀረት ያስችላል። በተጨማሪም ረቂቁ ምዝገባ ለሚያከናውኑ የፌዴራልና ክልል አካላት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን እና መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ እና በዝርዝር በማስቀመጥ፣ በእነዚህ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ለአስተዳደራዊ አካላትና ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚባልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ባለሥልጣኑ ማመልከቻ በቀረበለት በ30 ቀን ውስጥ ምዝገባውን ካላከናወነ መገናኛ ብዙሃኑ እንደተመዘገበ ተቆጥሮ ወደ ስራ መግባት እንደሚችል በመደንገግም ተጨማሪ ጥበቃ ተደርጎለታል።

የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን በሚመለከት ነባር ሕጎች ሁሉንም እኩል የሚያስተናግድና ሃሳብን የመግለፅ መብትን ለማረጋገጥ አስቻይ፣ ቀላልና ፍትሃዊ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከመዘርጋት አንፃር ክፍተቶች ነበሩባቸው። የፈቃድ ማመልከቻ የሚገመገምበት፣ ውሳኔ የሚሰጥበት ሒደት ፍትሐዊና ግልፅ አልነበረም የሚል ትችት ይነሳል። የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች ግልፅ ባለመሆናቸው ፈቃድ አሰጣጡ አድሏዊ እንደነበረ ባለድርሻ አካላት በጥናቱ ጊዜ በተደጋጋሚ አንስተዋል።

በረቂቁ የፈቃድ አመልካቾችን ለመለየት የሚያስችል መስፈርት፣ ማመልከቻው ሊያሟላ የሚገባቸው መረጃዎች፣ የሚሰጡ የፈቃድ አይነቶች፣ እና የፈቃድ ሁኔታዎች በዝርዝር ተደንግገዋል። በተለይም የብሮድካስት ፈቃድ መስፈርቶችና የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ይበልጥ ዘርዘር ብለው እንዲደነገጉ ተደርጓል። የፈቃድ መስፈርት ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል የፋይናንስ አቅም፣ ተአማኒነትና አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣የቴክኖሎጂና የቴክኒክ ብቃት፣ ድርጅታዊ ብቃት፣ ልምድና እውቀት ይገኙበታል። እነዚህ መስፈርቶች የተቀመጡት በመገናኛ ብዙሃን ስራ ለመሰማራት፣ ማሰራጫ ጣቢያውንና ስቱዲዮውን ለማቋቋም፣ ለማስተዳደር፣ ፕሮግራሞችን ለማምረት፣ ለመግዛት፣ ወይም

ባለሙያዎችን ለማስተዳደር ከፍተኛ የሆነ መነሻ ሃብት ስለሚያስፈልግ የተሻለ አቅም ያለው ባለፈቃድ በኃላፊነትና በብቃት የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ነው።

የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችም የተዘረዘሩ ሲሆን የሕዝብ፣ የንግድና የማኅበረሰብ ብሮድካስት አይነቶችም ተቀምጠዋል። ብዝሃነትን ለማበረታታትም ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቦርድ በማፀደቅ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ በሌሎች ባለፈቃዶች ያልተሸፈነ ወይም ትኩረት ያልተሠጠበት የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ለሚያመለክት አመልካች ልዩ የሕዝብ፣ የንግድ ወይም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጥ እንደሚችል ይደነግጋል።

የፈቃድ ማመልከቻ የሚገመገምበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ሒደት ፍትሐዊ እና ግልፅ እንዲሆን፣ሒደቱም ሕዝባዊ አስተያየቶችንና ግብአቶችንም የሚያስተናግድ ለማድረግ በረቂቁ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። በተለይም ውስን የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሲኖር ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾችን በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ፣ አግባብነት ባለውና ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን በሚገለጽ ማስታወቂያ የመጋበዝ ግዴታ ተጥሎበታል። በማስታወቂያ ለተደረገው ጥሪ ምላሽ ሊሰጡ ለሚችሉ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ እንዲሁም ለአመልካቾች ዝግጅት በቂ ጊዜ እንዲሰጥም ተደርጓል። ይህም አድሏዊ፣ ኢ-ፍትሃዊ እና የሙስና ተግባራትን ለመግታትና የባለሥልጣኑን ተአማኒነት ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው።

ክፍል አራት በሶስት ንዑስ ክፍሎች የመገናኛ ብዙሃን መብቶችን፣ ግዴታዎችን እና የፀዘት ግዴታዎችን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዟል። በተለይም ለመገናኛ ብዙሃን መብቶችና ነፃነቶች በግልፅ ጥበቃ የሚያደርጉና፣ ግዴታዎቻቸውን በኃላፊነት እንዲወጡ የሚያስችሉ አዳዲስ አንቀፆችም ተካተዋል፣ የነበሩ አንቀፆችንም በዝርዝር ለማብራራት ተሞክሯል።
የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች ሥራቸውን በነፃነትና በተጠያቂነት ማከናወን ይችሉ ዘንድ ሊጠበቁላቸው የሚገቡ መሠረታዊ መብቶች በአዋጁ ጥበቃ ተደርጎላቸዋል። **በተለይም በመገናኛ ብዙሃን የተሰራጨ ይዘትን ተከትሎ በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ጣልቃ ገብነት፣ ማስፈራሪያ፣ማዋከብና ሌሎች በመገናኛ ብዙሃን ነፃነትና በጋዜጠኞች ህልውና ላይ ስጋት የሚጥሉ ተግባራትን ለመከላከል ለመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ከለላ የሚሰጥ፣ በአጥፊዎቹ ላይም የተጠያቂነት አሰራር የሚዘረጋና እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ ግልፅ ድንጋጌ በረቂቁ እንዲካተት ተደርጓል። የዘርፉ ባለድርሻዎች** ፍትሕ የማግኘት፣ እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እና ማኅበር የመመስረት መብቶች ተገቢው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ረቂቁ ይደነግጋል።

ረቂቁ **የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ለመገናኛ ብዙሃን ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ እንደማይገደዱ ይደነግጋል። ይህ ጥበቃ ላይ ገደብ ማድረግን ከበድ ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲኖረው** ፍርድ ቤት በልዩ ሁኔታዎች መረጃ ለማግኘት የመረጃ ምንጭ እንዲገለጽ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ተመልክቷል። **ይህ አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያለው ጥበቃ ለጋዜጠኝነት ሙያ ካለው ከፍተኛ አስፈላጊነት አንፃር ለዘርፉና ለሕዝብ ጥቅም የተሰጠ ሲባል የተሰጠ ጥበቃ ነው።**

በረቂቁ መገናኛ ብዙሃን በዘገባዎቻቸውና ፕሮግራሞቻቸው ስህተት ሲሰሩ እርማት ወይም መልስ የመስጠት መብትን የማክበር ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል። ይህም ክስ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ቅሬታ አቅራቢውና መገናኛ ብዙሃን ችግሩን በራሳቸው እንዲቀርፉት እድል የሚሰጥ ነው። ይህ መብት በፍሬ ሃሳብ እውነተኛነት ላይ የተረጋገጠን ዘገባ በሐሰት ለማስተባበል ሊውል እንደማይገባም ተደንግጓል። በመደበኛው ጊዜና በምርጫ ወቅት እርማት ማውጣትና መልስ መስጠት ተግባራዊ የሚሆንባቸው ጉዳዮችና ሥነ-ሥርዓት ላይ ነባሩ አዋጅ የነበረበትን ክፍተት ለመሙላት፣ ምላሽ የሚቀርብበትን የጊዜ ሰሌዳና ኃላፊነት በግልፅ በማስቀመጥ ማሻሻያ ተደርጓል።

በረቂቁ በየጊዜው ለሚታተሙ ኅትመቶች **ወይም በይነመረብ መገናኛ ብዙሃን** ዋና አዘጋጅ እንዲሾምና፣ ዋና አዘጋጁም የሚታተሙትን ኅትመቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይታተም የማድረግ ሥልጣን እንዲኖረውና ለይዘቱም ሙሉ የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖረው ተደርጓል። በዋና አዘጋጁና በባለቤቶቹ መካከል የጥቅም ግጭትን ለማስቀረትና ባለቤቶች በ**ዋና አዘጋጁ ነፃነትና** በይዘት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ ለመከላከል የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች ወይም ውጤታማ ቁጥጥር ያለው የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ሰዎች ዋና አዘጋጅ ሆነው ከመሾም ተከልክለዋል። **ይሁንና** ረቂቁ **የባለሙያዎችን ባለቤትነት ለማበረታታት የመገናኛ ብዙሃን የባለቤትነት ድርሻቸው ከ25 በመቶ በታች የሆነ የመገናኛ ብዙሃን ሰራ የመስራት ፍላጎት ያላቸው ጋዜጠኞች ዋና አዘጋጅ መሆን እንዲችሉ ይፈቅዳል።**

በረቂቁ የሕዝብ፣ የንግድና የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የሚኖርባቸው ግዴታዎች በዝርዝር ተደንግገዋል። የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃንና ከሌሎች ምንጮች ይዘት የሚያሰባስቡ ወይም የሚያጠናቅሩና መልሰው የሚያሰራጩ አካላት እንዲሁም ይዘት የሚያነቡ ድረ-ገፆች የሚኖርባቸው ግዴታዎችም ተዘርዝረው ተደንግገዋል። በረቂቁ **እንደ ኬብል፣ ሳተላይትና ዲጂታል መልቲፕሌክስ አንቀሳቃሽ ያሉ የብሮድካስት አገልግሎት ይዘት የሚያስተላልፉ አካላት በበርካታ አገራት እንዳለው ይዘት ማመንጨት ሥራ ውስጥ መግባት እንደማይችሉ ተደንግጓል።**

በተለይ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች በተግባር የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ሆነው የማገልገል አዝማሚያ ስለነበራቸው የሕዝብ ጥቅምን መሠረት አድርገው የሃገሪቱን የቋንቋና የብሔር፣ የባህል፣ የኃይማኖት፣ **የዖታ፣ የክልልና** የፖለቲካ ብዝሃነት የሚያንጸባርቁ በተለይም **ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችንና** የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የማገልገል ግዴታዎች እንዳሉባቸው በግልፅ ተመልክቷል።

ረቂቁ ሀገራዊ ይዘት የማካተት ግዴታን በተመለከተ አዲስ ድንጋጌ ያካተተ ሲሆን ለሕዝብ፣ ለንግድና ለማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች እንዲሁም ለሃገራዊ፣ ክልላዊ አካባቢያዊ ሥርጭቶች **የፕሮግራም ኮታ መጠንንና** ከባለፈቃዶች ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ፕሮግራሞች ስለሚዘጋጁበት መንገድ **ያስቀምጣል። ይህ ድንጋጌ ሉላዊነት በሃገራዊ ባህል ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመገደብ ያለመ፣ የመገናኛ ብዙሃን ኅብረተሰቡ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲያድግ የማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚያስችል ነው።**

ረቂቁ የይዘት ግዴታዎችን የተመለከቱ በርካታ አንቀፆችንም አካቷል። እነዚህ ግዴታዎች መገናኛ ብዙሃን **የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዱ እንዲሆኑ፤ የሚያዘጋጁት ይዘትና ምንጭ እውነተኛና ትክክለኛ** መሆኑን የማረጋገጥ፣ የሌሎችን መብት በማይጥስ መልኩ እና ሕጋዊ ይዘቶችን የማሰራጨት ግዴታዎች በጥቅል

የተደነገጉ ሲሆን ሌሎች ዝርዝር ግዴታዎችን የያዙ አንቀፆችም ተካተዋል። በተለይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በሚመለከት ጥንቃቄ እንዲደረግና ጉዳት ያስከትላሉ የሚባሉ ይዘቶችን ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ሊመለከቱና ሊያዳምጡ በሚችሉበት ሰዓት ማለትም ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 11 እንዳያስተላልፍና ፕሮግራሞቹ ከመሰራጨታቸው በፊት **የፕሮግራሙን አድማጭ ወይም ተመልካች የዕድሜ ደረጃ አስቀድሞ በማሳወቅ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መረጃ መስጠት ይኖርበታል። ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን የሚያሰራጩ** የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶችም ለሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች ተገቢ ክብር እንዲሰጡና የሃይማኖት እና የእምነት ነጻነትንና መሠረታዊ ሰብዓዊ መብትን ባከበረ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ይገደዳሉ።

ከእነዚህም በተጨማሪ መገናኛ ብዙሃን በኃላፊነት መንፈስ ተግባራቶቻቸውን እንዲወጡ ለማስቻል በተለይም **በብሮድካስት አገልግሎት የሚሠራጩ ፕሮግራሞች የሚመሩበትን ዝርዝር የሥነ-ምግባር ደንብ ባለሥልጣኑ እንዲያወጣ ይደነግጋል። በሌሎች የተደራጀ የእርስ በርስ ቁጥጥር ባለባቸው ሀገሮች መገናኛ ብዙሃን የራሳቸውን የሥነ-ምግባር ደንብ የሚያወጡ ቢሆንም አሁን ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ የለም። ይሁንና ይዜንን በሂደት ለማረጋገጥ እንዲቻል ባለሥልጣኑ የሥነ-ምግባር ደንቡን ሲያዘጋጅና ሲተገብር የእርስ በእርስ ቁጥጥር ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አደረጃጀቶችን እንዲያሳትፍ እና በየሶስት አመቱ ግምገማ በማድረግ የእርስ በእርስ ቁጥጥር ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አደረጃጀቶች አጠቃላይ አሠራርና የሥነ-ምግባር ደንብ አፈጻጸም ይዞታ ውጤታማነትና ጥንካሬ አሳማኝ ደረጃ መድረሱን ሲያረጋገጥ ኃላፊነቱን ለእነዚህ አደረጃጀቶች እንዲያስተላልፍ በግልፅ ተደንግጓል።**

ረቂቁ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ እንዲመድቡ የሚያስገድድ ሲሆን አፈፃፀሙም ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በምርጫ ወቅት ብቻ ቢሆንም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ወቅትን ሳይጠብቁ በማናቸውም ጊዜ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሃሳብና አመለካከት እንዲያንሸራሽሩ ለማድረግና በተለይ በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን በፍትሃዊነት እንዲስተናገዱ የሚደነግጉ አንቀፆች እንዲካተቱ ተደርጓል።

በተጨማሪም መገናኛ ብዙሃን ካለባቸው ማኅበራዊ ኃላፊነት አንፃር የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚያናጋ ሁኔታ ወይም የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝቡን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ በሽታን በሚመለከት አስቸኳይ መንግሥታዊ መግለጫዎችን ሲኖሩ እንዲያሰራጩ ይገደዳሉ። ኃላፊነታቸውን ከማረጋገጥ እና ከመሰነድ አንፃርም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ማንኛውንም ያሠራጨውን ፕሮግራም ቀርጾ የማስቀመጥ እና በየጊዜው የሚወጡ ሳተመቶችም አግባብነት ላለው አካል ኮፒዎችን በነፃ እንዲያስቀምጡ ይገደዳሉ።

ከአፈፃፀም አንፃር በራስ አቅም ችግሮችን መፍታትን ለማበረታታት ረቂቅ አዋጁ ማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ከአንባቢ ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብን ቅሬታ ወይም አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድና ለመፍታት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ጥሎባቸዋል። በተጨማሪም መገናኛ ብዙሃን በአዋጁ የተቀመጡ ግዴታቸውን

ካልተወጡ ባለሥልጣኑ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ምክንያታዊ የሆነ የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችል የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁት የሚያደርግበት መንገድ በማስቀመጥ፣ እንደ ጥሰቱ ክብደት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎችም ሊወሰድ እንደሚችል ተደንግጓል።

ክፍል አምስት ባለሥልጣኑ ስለሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚመለከት ነው። በችግሮች ማመላከቻ ጥናቱ እንደተመለከተው በነባር ሕጎች የነበሩ አስተዳደራዊ ጥሰቶች በአግባቡ ሳይዘረዘሩ፣ የሚጣሉ ቅጣቶች የተጋነኑና ተመጣጣኝ ያልሆኑ እንደነበሩ እና ተቆጣጣሪው አካል የመገናኛ ብዙሃንን ነፃነት በሚገፋ መልኩ ይተገብራቸው እንደነበረ ለመለየት ተችሏል። በነባር ሕጎች ድንጋጌዎችን መጣስ እስከ ንብረት መወረስ እና ጣቢያውን ከነሙሉ መሳሪያው ሊያስወርስ የሚያስችል ቅጣት ይጣልባቸው ነበር። ስለዚህም በረቂቅ አዋጁ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ፍትሐዊ በሆነ መልኩ እንዲወሰዱ፣ የፍትሕ ሥነ-ሥርዓት እንዲከተሉና ቅጣቶችም ከጥፋቱ ክብደት እና ተደጋጋሚነት ጋር የተዛመዱ ተመጣጣኝ እንዲሆኑ የሚያደርጉ አንቀፆች ተካትተዋል።

በረቂቁ አዋጁ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን፣ አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብ ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ መገናኛ ብዙሃን የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች በሒደት እየጨመሩ እንዲሄዱ ተደርገዋል። በዚሁ መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች አራት አይነት ሲሆኑ እንደ መተላለፉ መጠን የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ እስከ 200 ሺህ ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት፣ ፈቃድ መታገድ እና ፈቃድ መሰረዝን ያጠቃልላሉ። ቅጣት አወሳሰኑ ላይ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው ሥርዓት ለመዘርጋት ቅጣት የሚያስጥሉ ድርጊቶች የተዘረዘሩ ሲሆን የቅጣት መጠኑ ጣሪያም እንዲቀመጥ ተደርጓል።

የገንዘብ ቅጣትን በሚመለከት በነባር ሕጎች የተደነገጉት የቅጣት መጠኖች ከመገናኛ ብዙሃን የገንዘብ አቅም አንፃር ተቋማቱን የመጥፋት አደጋ ላይ የሚጥሉ ስለነበሩ በረቂቁ አዋጁ **ባለሥልጣኑ የገንዘብ ቅጣት መጠን ሲወስን የመገናኛ ብዙሃኑን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታና በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሆንና ግዴታ ተጥሎበታል። ጣሪያውም** 200,000 **ብር እንዲሆን ተደርጓል። በዚህም የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ከአጠቃላይ ካፒታሉ አንጻር ሲሰላ የመገናኛ ብዙሃኑን ህልውና ከባድ አደጋ ላይ እንዳይጥል ተደርጓል።**

ይበልጥ ከባድ ለሆኑና በተደጋጋሚ ለተከሰቱ ጥፋቶች የፈቃድ እገዳና መሰረዝ ተግባራዊ እንደሚሆንም ተደንግጓል። ለእነዚህ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚዳርጉ ጥሰቶችም በግልፅ በረቂቁ አዋጁ ላይ ተካትተዋል። የመገናኛ ብዙሃንን የመከላከል መብት ለማስጠበቅም ለእነዚህ እርምጃዎች የሚዳርግ ክስ ሲቀርብ ባለፈቃዱ በጉዳዩ ላይ ያለውን ምላሽ በፅሁፍ እና በአካል እንዲያቀርብ መደረግ እንዳለበት በግልፅ ተደንግጓል። በተጨማሪም እነዚህ ውሳኔዎች ባለፈቃዱን ብቻ ሳይሆን የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎችና ደንበኞችን ጭምር ሊጎዱ ስለሚችሉ በጥንቃቄ እንዲወሰዱና የባለፈቃድንና የሕዝብ አስተያየትን ግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገቡ የሚያስገድዱ ድንጋጌዎች ተካተዋል።

በረቂቁ በእነዚህ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው አስተዳደራዊ ፍትህ የሚያገኝበትን እና ቅሬታዉ በአግባቡ የሚሰማበት ሁኔታም ተደንግጓል። በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ለቦርዱ ይግባኝ በማለት ውሳኔ ማግኘጥ ይችላል።

በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉዳዮችን በመመርመር አቤቱታ የመቀበልና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዲኖረው ተደርጓል። በተለይም ሂደቶቹ የተጋነነ ጊዜ እየወሰዱ የዘገየ ፍትህ መሰጠቱ ከመገናኛ ብዙሃን አንፃር ከፍተኛ ጉዳት ስለሚያስከትል ቦርዱም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ 30 ቀን ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጡ በመደንገግ የተፋጠነ ፍትህ እንዲገኝ ረቂቁ አቅጣጫ አስቀምጧል።

ከፍል ስድስት ሕጋዊ እርምጃዎች በተመለከተ የሚደነግግ ነው። **በመርህ ደረጃ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ሕግ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎችም ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑና ከይዘት ጋር የተያያዙ የወንጀልና የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችን ማካተት አይኖርበትም። ይሁንና በችግሮች ማመላከቻው እና ከአለም አቀፍ ተሞክሮ ለማየት እንደተቻለው በነባር ሕጎችና ሌሎች ሕጎች መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች አለም አቀፍ ሀሳብን በነፃነት መብት የደረሰበትን ደረጃ ያላማከሉና ለአስፈፃሚ አካላት ያልተገደበ መብት የሚሰጡ በመሆናቸው በሀገራችን ያሉ የመገኛኛ ብዙሃን ራሳቸውን እንዲገደቡና ለደሞክራሲያዊ አድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዳይጫወቱ ማደረጋቸው ተመላክቷል። ስለዚህም ረቂቅ አዋጁ ለመገናኛ ብዙሃን የተሻለ ጥበቃ ለማድረግ እንዲያስችሉ የሰም ማጥፋትና የአገዳ እርምጃን የሚመለከቱ አንቀፆችን አሻሽሏል።**

ሀገራችን በአለም አቀፍ መድረኮች በተደጋጋሚ የምትተቸው የሰም ማጥፋትን እንደ ወንጀል በመደንገጉ ነው። ሰም ማጥፋትን ወንጀል ማድረግ በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማት ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን የመገደቢያ መንገድ እንደሆነ በተደጋጋሚ አቋም የወሰዱ ሲሆን ብዙ ሀገራትም ይሄንን አስቀርተዋል። ረቂቁ አዋጁም ይሄንን በማሻሻል የሰም ማጥፋት የፍትሐብሔር እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት እንዳያስከትል ተደርጓል።

በነባሩ ሕግ ከወንጀል በተጨማሪ በሰም ማጥፋት ጉዳት የፍትሐብሔር ክስ ከተመሠረተ አስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) **የሚደርስ የህሊና ጉዳት ሊወሰን እንደሚችል ተደንግጓል። በረቂቅ አዋጁ ይሄንን ከፍ በማድረግ** የሰም ማጥፋትን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙሃን ላይ የሚጣለው የህሊና ጉዳት ካሳ ከብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ ብር) ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል። ከነባሩ ሕግ ሲነፃፀር የቅጣት መጠኑ ያደገ ቢመስልም ከዘርፉ እድገት፣ ከብር የመግዛት አቅም ማሽቆልቆልና የወንጀል ተጠያቂነት በመቅረቱ መገናኛ ብዙሃን በኃላፊነት እንዲሰሩ ከማድረግ አንፃር መጠኑ ማደጉ ተገቢ ይሆናል። ይሁንና የተቀመጠው መጠን ከፍተኛው ጣሪያ መሆኑንና የህሊና ጉዳት ካሳ ሲወሰን የመገናኛ ብዙሃንን የትርፍ ሁኔታ፣የደረሰው የጉዳት መጠን እና የሚወሰነው ካሳ በመገናኛ ብዙሃኑ ህልውና ላይ ያለው ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርበት ተመልክቷል።

በረቂቁ የሰም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነትን የማያስከትሉ ድርጊቶችና **ልዩ ሁኔታዎችም** ተዘርዝረው ተደንግገዋል። ከእነዚህም ውስጥ **በወንጀል ሕጉ የሰም ማጥፋት ወንጀል የሚሆነው የመጉዳት ሃሳብ ካለ መሆኑን ቢያስቀምጥም፣ በአዋጅ ቁጥር** 590/2000 **ግን የመጉዳት ሀሳብ ቢኖርም ባይኖርም በሐሰት መወንጀል የሰም ማጥፋት የፍትህ ብሔር ጥሰትን እንደሚያስከትል ተደንግጎ ነበር። ይህ በቅን ልቦና የሚፈጸምን ስህተትና መጠነኛ ስህተቶችን ስለሚቀጣ በተለይም ለፖለቲካ ንግግሮች የተሰጠውን ጥበቃ በሰፊው የሚጎዳ ነበር።** ስለዚህም ይህንን በማሻሻል የመጉዳት ሃሳብ

የሌለውን ይዘቱ እውነተኛ የሆነ ንግግር፣ በቅን ልቦና የተደረገ ንግግር እና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተደረገ ንግግር ከሆነ ተጠያቂነትን እንዳያስከትል ተደርጓል።

በተጨማሪም በነባር ሕጎች በሕገ መንግሥቱ በተቋቋሙ የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈጻሚ ወይም የፍርድ ቤቶች ባለሥልጣናት ላይ የሚፈጸሙ የስም ማጥፋትና በሐሰት የመወንጀል ክሶች የሚቀርቡት የግል ተበዳይ አቤቱታ ሳያስፈልጋቸው ነው። ይህም መገናኛ ብዙሃን ላይ የፖለቲካ ተፅእኖ እንዲኖር ከመፍቀዱም በላይ በወንጀል ሕጉ "የስም ማጥፋት ክሶች የሚቀርቡት በግል ተበዳይ አቤቱታ አማካይነት ነው" የሚለውን ድንጋጌ የሚጻረር ነው።ስለዚህም በረቂቁ ይህ እንዲቀር ተደርጓል።

የመገናኛ ብዙሃንን ውጤት እንዳይሰራጩ ወይም እንዳይተላለፉ የማገድ እርምጃ ለመንግሥት ከሚሰጠው ሥልጣን፣ በመንግሥት አካላት አለግባብ ሊገለገሉበት ስለሚችሉና ከቅድመ ምርመራ ጋር ይመሳሰላል በሚል መገናኛ ብዙሃኑ ተጠያቂ ሊደረጉ የሚገባው ሕግ ተላልፏል የተባለው ይዘት ከተሰራጨ በኋላ መሆን አለበት የሚሉ አካላት አሉ። በተቃራኒው በጣም በተለየ ሁኔታ አንድ የጎተመት ወይም ሌላ የመገናኛ ብዙሃን ስራ የሕዝብን ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚጥል እና ግልፅ እና ቅርብ አደጋ (Clear and Present Danger) ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ሲገመት ጉዳቶችን ቀድሞ ለመከላከልና የሰዎችን ህይወት ለመጠበቅ የእገዳ ክልከላ መኖር አለበት የሚሉና ይሄንንም የደነገጉ ሀገራት አሉ። በእነዚህ ሀገራትም የእገዳ እርምጃዎች የሚፈቀዱት በልዩ ሁኔታና የተለያየ ከባድ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ የተሟሉ እንደሆነ ብቻ ነው። ከእነዚህም መካከል በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንጂ በባለሥልጣናቱ ፍላጎት የሚፈጸም እንዳይሆን መከልከል፣ ወንጀሉ ወይም አደጋው የመድረስ እድሉ ከፍ ያለ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ዓቃቤ ሕግ ላይ እንዲወድቅ ማድረግ እና አደጋው ከሥርጭት በኋላ በመቅጣት የሚቀለበስ አለመሆኑን የማረጋገጥ ግዴታን መደንገግ ተጠቃሽ ናቸው።

በነባር ሕጎች የእገዳ እርምጃ ተደንግጎ የነበረ ቢሆንም ከላይ የተቀመጡ ስጋቶችን በአግባቡ በሚመልስ መልኩ የተቀመጡ አልነበረም። ለምሳሌ አደጋውን የማስረዳትና የሚሰራጨው ይዘት አደጋ እንደሚያስከትል የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 590/2000 አልተደነገገም። በአተገባበሩም ግልጽ የሆነ ሥነ-ሥርዓት ስለልነበረው በመንግሥት አካላት አለግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ መገናኛ ብዙሃንን ለጫና እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ የዳረገ ነበር።

በሀገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የእገዳ እርምጃን ሙሉ ለሙሉ ማስወጣት አስቸጋሪ እንደሆነ በመገንዘብ በረቂቅ አዋጁ የእገዳ እርምጃዎች የሚወሰዱበትን ሁኔታ እና ሂደት ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር የተስማማና አላግባብ እንዳይተገበር ጥበቃ የሚያደርጉ ግልፅ አንቀፆችን ባካተተ መልኩ ተሸሽሏል። በረቂቁ እንደ ነገሩ ሁኔታ የፊዴራል ወይም የክልል ዓቃቤ ሕግ በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልፅና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ሕገወጥ ጎተመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት

ሲኖረው የጎትመት ውጤቱ ወይም የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲያዝ ማመልከት እንደሚችል ተደንግጓል።

ይሁንና **ዓቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ የውሳኔ ሰጪውን ደረጃ ከፍ በማድረግ በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ውሳኔ** በየጊዜው የሚወጣ ጎትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ **ትእዛዝ ሊሰጥ** እንደሚችል ተደንግጓል። ይህም ማንኛውም የመንግሥት አካል በዘፈቀደ እገዳ ውሳኔን እንዳይወስን ይከላከላል። ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን **በ48 ሰዓት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማስታወቅ እንዳለበትና እግዱ በ48 ሰዓት ለፍርድ ቤት ካልቀረበ እንደተነሳ እንደሚቆጠር ተደንግጓል። ተጠያቂነትን ለማስፈንና ኃላፊነትን ለመጨመርም ይሄንን ሥልጣን ዓቃቤ ሕግ አግባብ በሌለው መንገድ የተጠቀመበት እንደሆነ በሕግ እንደሚጠየቅ፤ አለግባብ መጠቀማቸው የተረጋገጠ የመንግሥት አካላት የሆኑ ግለሰቦች ላይም አስተዳደራዊና የገንዘብ ቅጣት ሊጣል እንደሚችል እና በእገዳው ምክንያት** መገናኛ ብዙሃኑ ለደረሰበት ጉዳት አግባብነት ባለው ሕግ መንግሥትን የሞራል እና የጉዳት ካሳ ሊጠይቅ እንደሚችል ተካቷል።

በዚህ ክፍል ረቂቁ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዙ ክሶች ስለሚቀርቡበትና ስለሚሰሙበት እና ስለይርጋ ሥነ-ሥርዓትም ድንጋጌዎችን አካቷል። እነዚህ ድንጋጌዎች በሌሎች አገሮች በመደበኛ የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ስለሚመሩ የተለመዱ ባይሆንም ለመገናኛ ብዙሃን የተሻለ አስቻይ ሁኔታ ስለሚፈጥሩ ተሻሽለው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። በእነዚህ አንቀፆች የሕግ ሂደቶች በመገናኛ ብዙሃን ላይ አላስፈላጊ ጫና እንዳያሳድሩ ለማድረግና የተፋጠነ ፍትህ እንዲገኝ ለማስቻል የታለሙ ናቸው።

በማጠቃለያ ክፍል ሰባት በሌሎች ክፍል የማይካተቱ ወይም የተለመዱ የአዋጁ **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች አስቀምጧል። በዚህ መሠረት የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፣ የመብትና ግዴታ መተላለፍ፣ የባለሥልጣኑ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣ ስለተሻሩ ሕጎች፣ ተፈጻሚነት ስላላቸውና ስለሌላቸው ድንጋጌዎች እና አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ የሚደነግጉ ናቸው።** ረቂቅ አዋጁ ነባሩን የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ሙሉ በሙሉ በሚተካ ሁኔታ የተዘጋጀ በመሆኑ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999ን እንዲሻር ያደርጋል። ነገር ግን **በአዋጅ ቁጥር 590/2000 ተካተው የነበሩ በረቂቁ እንዳይካተቱ የተደረጉ የመረጃ ነፃነት ድንጋጌዎች አሉ። እነዚህ ድንጋጌዎች ራሱን በቻለ አዋጅ ተሻሽለው እንደሚወጡ ይጠበቃል።**

ባለሥልጣኑ አዋጁን ለማስፈጸም የሚያወጣቸው ብዛት ያላቸውን የአፈጻጸም መመሪያዎች በቦርድ ማስጸደቅ ይጠበቅበታል። የብሮድካስት አገልግሎትን ማስተዳደር ውስብስብና በርካታ በየጊዜው የሚለዋወጡ ጉዳዮችን የሚያካት በመሆኑ በአዋጁ ሁሉንም በማካተት መደንገግ አዳጋች ነው። በመሆኑም በአዋጅ ጥቅል ድንጋጌዎችንና መርሆችን በማስቀመጥ ተቆጣጣሪ ተቋማት ዝርዝር መመሪያዎችን በማውጣት ከጊዜው ጋር የሚሄዱ ለውጦችንና ማሻሻያዎችን እንዲያደርጉ በመፍቀድ፣ መመሪያዎች አሳትሞ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ እና በሚዘጋጁበት ጊዜም ሕዝባዊ መድረኮችን በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ግብዓት መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል።